# ወንጌላዊነት በኦርቶዶክስ

ወንጌላዊነት የሚለውን ቃል ጥቅም ላይ ያዋልኩት “Evangelicalism” የሚለውን ኢንጊሊዘኛ ቃል ለመወከል ነው ፤ ለምን “ወንጌላዊነት” አላልከው? ለሚል ሰው ወንጌላዊነትን የሚለውን ቃል በዚህ ጽሑፍ ላይ በአሉታዊ ትርጉም ስለምጠቀመው “ወንጌላዊነት” የሚለው ቃል የዚህ አሉታዊ እንቅስቃሴ ሰለባ እንዳይሆን ነው።

ወንጌላዊነት ምንድነው? ወንጌላዊነት በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከአሜሪካ ፕሮቴስታንቶች ውስጥ የወጣ እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴ 1ኛ እና 2ኛው ታላቅ መነቃቃት (The great awakenings) በሚባሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የወጣ ሲሆን የአሜሪካን ብቻ ሳይሆን የዓለምን ፕሮቴስታንት (እንዲሁም ክርስትናን) አናውጧል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ሳይነሱ በፊት በአሜሪካ ውስጥ የተመሠረቱት ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ትውፊታዊ እና ሥርዓታዊ የሆነውን ቅዳሴያዊ ሥርዓተ አምልኮ ይከተሉ ነበር ፤ ከመጥምቃዊት ቤተክርስቲያን ውጪ ያሉት ሁሉም ሕፃናትን ያጠምቁ ነበር ስለዚህ አብዛኞቹ አማኞች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በክርስቲያናዊው ሥርዓት ያደጉ ነበሩ። ነገር ግን እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በአሜሪካ ባሕል ውስጥ ጥብቅ ቦታን ከያዙ በኋላ “የስም ክርስቲያኖች” መብዛት ያዙ ፤ ከሕፃንነታቸው ተጠምቀው በቤተክርስቲያን ውስጥ ስላደጉ እንደ ወላጆቻቸው የሚያስታውሱት “ዳግም የመወለድ ጊዜ” (Born again experience)የላቸውም። በዚህም ምክንያት ብዙ መጋቢዎች ቤተክርስቲያኒቷ “ዳግም ባልተወለዱ ክርስቲያኖች” እየተሞላች ነው የሚል ስጋት እያደረባቸው መጣ። ለዚህም ሲሉ እንደ ጆናታን ኤድዋርድ ፣ ጆርጅ ዋይትፊልድ አይነት መጋቢ ሰባክያን መነሳት ጀመሩ። እንዲሁም በዚህ ጊዜ “ተንቀሳቃሽ ሰባክያን” የተባሉ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ፣ የሰውን ስሜት የሚያስነሱ ፣ ክርስቲያኖኢችን ከተኙበት የሚያነቁ ሰባክያን መነሳት ጀመሩ። ይህ እንቅስቃሴ በወቅቱ ለነበሩ ፕሮቴስታንቶች ራሱ እንግዳ ነበር እነርሱ ልክ እንደ ኦርቶዶክስ እና ካቶሊክ የራሳቸው ሐገረ ስብከት የነበራቸው እና በተሾሙ መጋቢዎች እና በሲኖዶሳት የሚመሩ ነበሩ። ነገር ግን ይህ የመነቃቃት እንቅስቃሴ ሁኔታውን እየለወጠው መጣ ፤ ተንቀሳቃሽ ሰባክያን እየበዙ መጥተው ቀድሞ የነበሩ ሐገረ ስብከቶች እየተጣሱ መጡ ፣ ሥርዓታዊው ቅዳሴያዊ አምልኮ ይበልጥ ወደ ስሜት ቀስቃሽ የአምልኮ መንገድ እየተለወጠ ሔደ ፣ ስብከቱም እውቀት ካለው ሰባኪ ይልቅ ስሜትን የሚነካ እንዲሆን ብቃት ባለው ካሪዝማቲክ ሰባኪ እንዲሰጥ እየሆነ ሔደ። ቤተክርስቲያንም “ዳግም ባልተወለዱ ክርስቲያኖች” እየተሞላች ነው የሚለው ትልቅ ስጋታቸው ስለነበር “ጌታን የመቀበል” ወይም “ዳግም የመወለድ ጊዜ” ይበልጥ ትኩረት ይሰጠው ነበር ስለዚህም ከልጅነቱ ተጠምቆ በክርስትና ውስጥ ያደገ ሰው ላይ ጥርጣሬ ይደረግበታል የሆነ ዳግም ተወልድኩ ፣ ጌታን ተቀብልኩ የሚልበት ልዩ ስሜታዊ ጊዜ እንዲኖረው ይጠበቃል። እንግዲህ እነዚህን በመሳሰሉ ሁኔታዎች ነበር ወንጌላዊነት የተወለደው።

ወንጌላዊነት በአማሪካ ውስጥ በዚህ ሁኔታ ከተወለደ በኋላ እንደ እሳት በዓለም ሁሉ ውስጥ ተስፋፋ ፣ ያልነካው የፕሮቴስታንት ክፍል የለም ነገር ግን በፕሮቴስታንት ብቻ አላበቃም በትንሹም ቢሆን ካቶሊክ እና ኦርቶዶክስን መንካቱ አልቀረም። አሁን ላይ ወንጌላዊነት ከሚታወቅባቸው ዋነኛ መለያዎቹ መካከል ሥርዓታዊ እና ትውፊታዊ የሆኑትን የቤተክርስቲያን አስተዳደርም ሆነ ቅዳሴያዊ አምልኮ ትቶ ስሜታዊ እና ዘመናዊ አምልኮን መተግበር እንዲሁም ልዩ የሆነ “ዳግም የመወለድ ሁነት” (በሐገራችን ጌታን የተቀበልኩበት ጊዜ) መያዙ ነው። ለምሳሌ ሥርዓተ አምልኮውን ብናይ በአንድ እሑድ አንድ ወንጌላዊ አማኝ ወደ ቤትተክርስቲያን ይሔዳል ፣ ስሜታዊ በሚባለው እና በዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ በታጀበው መዝሙር ይሳተፋል ፣ ደግሞም ይህ መዝሙር በየ ጊዜው ካላንደር የተስማማ ተደርጎ የተበጀ ሥርዓታዊ መዝሙር አይደለም ያን ቀን “የአምልኮ ባንድ” የመረጠው መዝሙር ይዘመራል ፣ ከዚያም ዋና ቦታ በሚሰጠው በስብከት ጊዜ ይሳተፋል ፣ ይሄም ቢሆን ስሜትን ሚያሚሙቅ (emotionally charged) የሆነ ንግግር አይጠፋውም ከዚያም በመዝሙር እና በጸሎት በመጨረስ ወደ ቤቱ ይመለሳል።

ይህንን የአምልኮ ጊዜ ከታሪካዊው ክርስትና ሥርዓተ አምልኮ ጋር ስናወዳድረው ፍጹም የተለየ ሆኖ እናየዋለን። ታሪካዊ ክርስትና ሥርዓተ አምልኮውን የሚመራው በቅዳሴያዊ አምልኮ ሥርዓት ነው። ዓመቱን ሙሉ የትኛው ጸሎት መባል እንዳለበት ፣ የትኛውም መዝሙር እንደሚዘመር ፣ የትኛው የመጽሐፍ ክፍል እንደሚነበብ ፣ ስብከቱ ከየትኛው ክፍል እንደ ሆነ ተቀናኝቶ በካላንደር የተቀመጠ ነው ስለዚህ አንድ መጋቢ መጥቶ የፈለገውን ሥርዓት መርቶ የሚወጣ አይደለም። እዚህ ላይ የሚቀርቡ መዝሙራትም ረጋ ያሉ እና የቤተክርስቲያኒቱን ነገረ መለኮት በጥንቃቄ የሚያስተምሩ ናቸው። ይህ የመጀመሪያው ክፍል የቃሉ ቅዳሴ (Liturgy of the Word) እየተባለ ይጠራል ዋና ዓላማው ክርስቲያኖችን የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ነውና ለዚህም ነው የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚነበቡት ከዚያም ከነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቄሱ ስብከት እንዲሰጥ የሚደረገው። የቃሉ ቅዳሴ የሥርዓተ አምልኮው ጅማሬ ነው እንጂ ፍጻሜው አይደለም የሥርዓተ አምልኮው ፍጻሜ የቁርባን ቅዳሴ (Liturgy of the Eucharist) ነው። ቄሱ በካላንደሩ መሠረት የዕለቱን የቁርባን ምስጋና (Anaphora) ያነባል አብዛኞቹ የቁርባን ምስጋናዎችም የድኅነትን ታሪክ የሚዘግቡ ናቸው ማለትም ወደ ወደቅንበት ውድቀት ክርስቶስ መጥቶ ፣ ስለ እኛ እንደ ሞተ ፣ እንደ ተነሣ ፣ ወደ ሰማያት እናረገ ፣ ዳግም በክብር እንደሚመጣ። (ነገር ግን  በብዙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህ ክፍል ቄሱ ለእግዚአብሔር አብ ክርስቶስን እያቀረበ እንዳያስመስል አጥሮ ይገኛል)። ከዚህም በኋላ የቁርባን መመሥረት ሁነት (The institution narrative) በይፋ ይታወጃል ፣ ሕዝቡም አሜን እያለ ይቀበላል። ይህ ሁነት ክርስቶስ ቁርባንን የመሠረተበትን ዕለተ ሐሙስ የሚያውጅ ነው “ሕብስቱን ባረከ ፣ ቀደሰ ፣ አመሰገነ ፣ ቆረሰ ፣ ሰጣቸው” የሚሉ ቃላት ሲኖሩት እንዲሁም “ጽዋውን ባረከ፣ ቀደሰ ፣ አመሰገነ ፣ ሰጣቸው” የሚሉትን ቃላት ካወጀ በኋላ “ይህ ስለ እናንተ የሚቆረሰው ሥጋዬ ነው” “ ይህም ስለ እናንተ ለኃጢአት ሥርየት የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው” በመባል ይታወጃል። ከዚህም በመቀጠል ክርስቶስ “ይህን

ኅብስት በበላችሁ ጊዜ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ እስክመጣ ድረስ ታስቡኛላችሁ” ብሎ እንደተናገረ ፤ የሞቱ እና የትንሣኤው መታሰቢያ (Anamnesis) ይደረጋል። በመጨረሻም ሕብስቱ እና ወይኑን እንዲቀድስ መንፈስ ቅዱስ ይጠራል (Epiclesis) ቁርባኑም ለሕዝቡ ተዳርሶ በምስጋና ይዘጋል።

ነገር ግን በታሪካውያን ፕሮቴስታንቶች (አንግልጣራውያን ፣ ሉተራውያን ፣ ቀሳውስታውያን)[1] ሁል ጊዜ የቃሉ ቅዳሴን ተከትሎ የቁርባን ቅዳሴ አይኖርም። ይህም የሆነበት ምክንያት የተሐድሶው እንቅስቃሴ በተነሳ ጊዜ አብዛኛው የካቶሊክ ምዕመን ቁራቢ አልነበረም ስለዚህ ብዙህ ጊዜ የሚቅርቡት ቀዳሾቹ ቀሳውስት ብቻ ይሆናሉ። አነ ሉተር ግን ይህንን ተቃወሙ ቁርባን ኅብረታዊነት ነው እንጂ ቄሱ ለብቻው የሚፈጽመው ነገር አይደለም በማለት በዕለቱ የሚቁርብ ሰው ከሌለ ሥርዓት አምልኮው በቃሉ ቅዳሴ ብቻ እንዲቆም አስደረገ። ይህንን ተከትሎ በሉተራውያኑ ዘንድ በአብዛኛው የቁርባን ቅዳሴ የሚኖረው በወር አንድ ቀን ብቻ ሲሆን ሌሎቹን እሑዶች የቃሉን ቅዳሴ ብቻ ፈጽመው ይለያያሉ። በቀሳውያውያኑ እና በሌሎቹ ተሐድሶአያን ዘንድ ደግሞ የቁርባን ቅዳሴ በ3 ወር አንድ እሑድ ላይ ብቻ እንዲሆን ሆኗል። እንዲሁም የፕሮቴታንት ሐዳስያን የቃሉ ስብከት ላይ በጣም ያተኩሩ ስለነበር ፤ ስብከት እንዲሁ የምሥጢር ማሚማቂያ ብቻ ሳይሆን በራሱ ምሥጢር ደረጃ እስኪታይ ድረስ ከፍ ብሏል። ከዚህ የተነሣ ከፕሮቴስታንት ተሐድሶ የተውጣጡት አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛውን እሑዶች የሚያሳልፉት ቃሉን በመስበክ ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና በመዘመር ብቻ ነበር። እንግዲህ ወንጌላውያን ይሄንን መሠረት ይዘው ሥርዓቱን በመተው ትንሽ ስሜት ጣል በማድረግ ፣ ዘመናዊ መዝሙራትን በመጨመር አሁን ላይ አንድ መካከለኛ ኢትዮጵያዊ የወንጌል አማኝ የእሑድ አምልኮውን የሠሩት።

ወደ ቀድሞ ነገር እንመለስ ወንጌላዊነት አመጣጡ ይህ ከሆነ ታድያ “ወንጌላዊነት በኦርቶዶክስ” ርእሱ ላይ ያልነው ምን ሆነን ነው? ማስተዋል ያለብን ወንጌላዊነት በራሱ ቤተእምነት ሳይሆን እንቅስቃሴ መሆኑን ነው ፣ ይህ እንቅስቃሴም የብዙህ ቤተእምነቶች አጥር ገርስሶ ገብቷል። የፕሮቴስታንት ቤተ እምነት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ቅዳሴያዊ ሥርዓተ አምልኮውን ይዞ ቢገባም በወንጌላዊነት ማዕበል መነካቱ አልቀረም ፤ ለዚህም አንዱ ማሳያ ሉተራዊ መሠረት ያላት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት[2] ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ናት። መካነ ኢየሱስ አሁንም ድረስ ቅዳሴያዊ ሥርዓቷን አስጠብቃ ብትገኝም አብዛኛው ማኅበረ ምዕመኗ ግን የኢትዮጵያን ጴንጤ ወንጌላዊ ሥርዓተ አምልኮ ይከተላል ፤ ወንጌላዊነት የቤተ እምነት ድንበርን መጣሱን የምናየውም አንድ በሙሉ ወንጌል ያደገ አማኝ መካነ ኢየሱስ እና መሠረተ ክርስቶስ ቢሔድ እንደ ቤቱ ስለሚሰማው ነው።

---

[1] Anglicans, Lutherans and Presbyterians

[2] ወንጌላዊት ያላልናት ስትመሠረት ወንጌላዊት ብቻ በመሆኗ ነበር አሁን ላይ ግን ወንጌላዊት ብንላት የተገባት ስም መሆኑ አያጠራጥርም።

ነገር ግን ይህ ወንጌላዊነት በኢትዮጵያ ፕሮቴታንት ቤተ እምነቶች ብቻ ተወስኖ ያለ ነው አይደል? አይደል? አይደለም!
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንም በዚህ ወንጌላዊነት እሳት ተጠቅታ ሕዝቧ ከታሪካዊው ቅዳሴያዊ ሥርዓተ አምልኮ ርቋል!

ይህ እንዴት ነው ካልን አንዱ እና ትልቁ ማሳያ የእሑድ ሥርዓተ አምልኮዋችን እንዴት እንደሚተገበር ማሳየት በቂ ነው። የኢኦተቤ የዕለተ እሑድ ሥርዓተ አምልኮ አንድ ሳይሆን ሁለት ነው ፡ ቅዳሴያዊ እና ወንጌላዊ። የእሑድ ቅዳሴ ካለቀ በኋላ የዕለቱ ቅዳሴ ተጠናቋል ተብሎ ሕዝቡ ወደ ቤቱ አይሸኝም ይልቅስ በውጪ ወንጌላዊ መርሐ ግብር ይደረጋል እንጂ። በውጪውም የሚዘመሩት መዝሙራት ሥርዓተ አምልኮአዊ ፣ ቅዳሴያዊ ሳይሆኑ ዘመናዊ እና በአብዛኛው ስሜታዊ መዝሙራት ናቸው። በአብዛኛውም እነዚህ መዝሙራት ዘማሪው እንደ ፈቃዱ ደስ ያለውን የሚዘምራቸው መዝሙራት ናቸው እንጂ ከቅዳሴያዊው ካላንደር ጋር እንኳን ላይገናኝ ይችላል። ከመዝሙሩ በኋላም ረዘም ያለ ስብከት ልክ እንደ ወንጌላውያኑ በስሜት የታጀበ ይሰጣል ፣ ከስብከቱ በኋላም ረዘም ላለ ሰአት ገቢ ማሰባሰቢያ በማድረግ በመዝሙር እና በጸሎት ይዘጋል። ከዚህ የተነሣ በአንድ ኢኦተቤ ቤተክርስቲያን የእሑዱን አገልግሎት ካየነው ከሌሊቱ 11 ሰአት እስከ ቀኑ 4 ሰአት ድረስ ሊረዝም ይችላል ይህ በየትኛውም ቤተክርስቲያን የማይታወቅ የጊዜ ርዝማኔ ነው።

ይህ የጊዜ ርዝመትም ስለሚታወቅ ቀሳውቱ አንድ አንድ የራሳቸውን እርምጃዎች እየወሰዱ ይገኛሉ ይህም ቅዳሴውን አፈጣጥኖ ቶሎ መጨረስ እና ሰው በማይመጣበት ሰአት በሌሊት መጀመር ሆኗል። በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ቅዳሴው ከ10፡30 እስከ 11፡30 ባለው ሰአት ይጀመራል። ይህ ደግሞ ከቅዳሴ በፊት ያለው ስብሐተ ነግህ እና ኪዳን ሳይታሰብበት ነው።[3] ቅዳሴውም ጀምሮ መልእክታት ይፋጠናሉ ፣ ይዘለላሉ። እንዲሁም ከላይ ሥርዓተ ቅዳሴውን ስንገልጽ የቁርባን ምስጋና ላይ ያሉ ብዙህ ጸሎቶችን ቄሱ ልብቻውን በራሱ ይጸልያቸዋል ፣ ከዚህ የተነሣ አብዛኛው ሕዝብ ቁርባን የተሠራባቸው ቃላት ሲታወጅ ፣ የቁርባኑን መታሰቢያ አይሰማም። እንዲህ እየተደረገ ቅዳሴው ቶሎ ይጠናቀቅ እና የውጪው ወንጌላዊ መርሐ ግብር ዋናውን ቦታ ይይዛል።

ይህ አተገባብር ለምዕመኑ ቅዳሴው እንዲሁ መተገበር ስላለበት ብቻ (for formality) በፍጥነት ይደረግና ዋናው የእሑድ ሁነት የውጪው ወንጌላዊው መርሐ ግብር እንደሆነ ያስተምረዋል። ቅዳሴውማ ደባሪ ቶሎ ማለቅ ያለበት ሥርዓት ነው ዋናው ዘመናዊ አማርኛ መዝሙራትን መዘመር እና ስብከት ነው። ይህን እውነታ የቤተክርስቲያኒቱን ምዕመናን አይተን ብቻ ማወቅ እንችላለን ፣ አብዛኛው ምዕመን የቤተክርስቲያኒቱ ዋና

---

[3] ይህ አገልግሎት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት Matins እየተባለ ይጠራል እናም የቅዳሴን ሰአት ሲያሳውቁ ይህንን ማቲንስ በመጨመር ጭምር ነው። በእኛ ቤተክርስቲያን ስብሐተ ነግህ ይጨመርበት ካልን ሌሊት 9እስከ 10 ላይ ቢጀመር ነው።

ሥርዓተ አምልኮ ላይ የማይሳተፍ ነው፣ አልመሳተፍ ብቻ አይደለም አያውቀውምም ጭምር እንጂ። የቤተክርስቲያን አባልነቱን የሚያውቀው "በሚወደው ዘማሪ ፣ በሚያደንቀው ሰባኪ ፣ በሚወደው መዝሙር" በኩል ነው። ማለትም የምዕመኑ ዋና ቤተክርስቲያናዊ ሁነት ቅዳሴ ሳይሆን መዝሙር እና ስብከት ነው። በዚህ አኳኋን ከአንድ ወንጌላዊ አማኝ የቤተክርስቲያን ሕይወት ፣ የአንድ ኦርቶዶክሳዊ የቤተክርስቲያን ሕይወት የሚለይ አይደለም።

አሁን ላይ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁለት አይነት ምዕመን ተፈጥሯል፡ ቅዳሴያዊ ምዕመን እና ወንጌላዊ ምዕመን። ቅዳሴያዊው ምዕመን በቁጥር የሚያንሰው እና ለቅዳሴ በጠዋት 10:30 አከባቢ ቤተክርስቲያን የሚደርሰው ሲሆን ፣ ከቅዳሴ ተሳትፎው የተነሣ የቤተክርስቲያኒቱን የሥርዓተ አምልኮ ሕይወት ያውቀዋል። ነገር ግን ለቅዳሴ በሌሊት ስለመጣ ከድካም የተነሣ የውጪውን መርሐ ግብር መሳተፍ ይከብደዋል ስለዚህም ስይሸኝ ወደ ቤቱ ይሔዳል። ሌላኛው ደግሞ በቁጥር የሚበዛው ወንጌላዊ ምዕመን ነው ፤ አብዛኛውን ጊዜ ቅዳሴ መሐል ላይ አልያም ሲያልቅ ይመጣል መዝሙር ይዘምራል ስብከት ሰምቶ ወደ ቤቱ ይሔዳል ፤ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ የአምልኮ ሕይወትም በአብዛኛው አያውቅም።

በዚህ ሁኔታ እንግዲህ ወንጌላዊነት በኦርቶዶክስ ተንሰራፍቶ ይገኛል!